የኢትዮጵያ ዘውድ ምክር ቤት

THE CROWN COUNCIL OF ETHIOPIA

HIS IMPERIAL HIGHNESS PRINCE ERMIAS SAHLE-SELASSIE HAILE-SELASSIE
PRESIDENT

በመጀመርያ፣ ከሁሉም አስቀድሜ፣ ለአምላካችን ክብርና ምስጋና ይግባው ለማለት እፈልጋለሁ። ከዚህ በመቀጠል፣ እንኳን ሁላችንም ለጎንደር ሆስፒታል መቶኛና ለጎንደር ዮኒቨርስቲ ሰባኛ ዓመት የምስረታ በዓል አደረሰን። ዛሬ በመሃላችሁ ተገኝቼ የደስታው ተካፋይ እንድሆን እንደ አንድ የአጼ ኃይለ ሥላሴ የቤተሰብ አባል በማክበር የጋበዙኝን ዶ/ር ያሬድና ዶ/ር ኑሩን ከልብ አመሰግናለሁ። የጎንደር ዮኒቨርስቲ ፕረዝደንት ዶ/ር አስራት አጸደ-ወይንም የዮኒቨርስቲው አዳራሽ በቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ስም መሰየሙን በደብዳቤ ስላስታወቁኝም እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።

በመላው አገራችን አጼ ኃይለ ሥላሴ የትምህርት ተቋማት በመገንባት፣ በዕውቀት የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመፍጠር ብዙ ደክመዋል። ይሁን እንጂ፣ አብዛኛዎቹ ተቋማት አጼ ኃይለ ሥላሴን ለመዘከር ጎንደር ዮኑቨርስቲ ያገኘውን ዕድል ገና አላገኙም። ስለዚህም፣ የጎንደር ዩኒቨርሲቲን ፈለግ ተከትለው ሌሎቹም የአጼ ኃይለ ሥላሴን መልካም ስምና ተግባር ወደፊት እንደሚዘክሩ ተስፋ እናደርጋለን።

መቼስ፣ እንደ ጎንደር ሆስፒታልና ዮኒቨርስቲ፣ የመቶና የሰባ ዓመት ታሪክ ላላቸው ተቋማት፣ እውቅና ሰጥተን ማክበር ከቻልን፣ ከሶስት ሺ ዘመን በላይ ዕድሜ ላላት የአገራችን ታሪክ፣ ባህልና የህዝባችን አንድነት ተገቢውን ክብር ለመስጠት ያቅተናል ብዬ አላስብም። ሁሉም ያለፈበትን ታሪክ በአግባቡ ሲያከብር ደስ ይላል። ዛሬ እኮ ደስ ብሎን የተሰበሰበነው የጎንደር ዮኒቨርስቲና የሆስፒታሉን ታሪክ ስላከበርን አይደል? ወደፊትም ብዙ የምናከብራቸው የጋራ ታሪኮች ስላሉ የሁላንችም ሰላም፣ ፍቅር፣ መቻቻልና መተባባር ወሳኝ ነው።

በመጨረሻው ማንሳት የምፈልገው፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው እጅግ የሚያሳስብ የጤና አገልግሎት ጉዳይ ነው። በርካታ ኢትዮጵያዊያን ሃኪምና የጤና

ባለሙያዎች፣ በበጎ ፍቃደኛነት፣ አገርና ሕዝባችንን የምታገለግሉ እንዳላችሁ አውቃለሁ፤ ነገር ግን፣ ኢትዮጵያ ዉስጥ ካለው የጤንነት አገልግሎት ተፈላጊነት አንጻር በቂ ነው ማለት አንችልም። ከሌላ አንጻር ደሞ፣ በበጎ አድራጎት ዘርፍ፣ አገራችንንና ሕዝባችንን ተጠቃሚ ለማድረግ አስፈላጊውን ትብብር ብናደርግላቸው መልካም ነው እላለሁ።

በዚህ ረገድ፣ የኢትዮጵያን ጥንታዊ የዘውድ አስተዳደርና ባህል በዓለም አቀፍ ደረጃ ከማስተዋወቅ አልፎ በበጎ አድራጎት ዘርፍ የበኩሉን ሚና ለመጫወት የሚፈልገው የኢትዮጵያ ንጉሣዊ በጎ አድራጎት ባለ አደራ ድርጅት ወይም Royal Ethiopian Trust (RET)፣ ከአንዳንድ የጤና ባለሙያዎች ጋር ተባብሮ ለመስራት ይፈልጋል። RET በቅርቡ ከመቅደላ በኢንግሊዞች ተዘርፎ የነበረውን የአጼ ቴዎድሮስን ጋሻ በክብር ወደ አገሩ እንዲመለስ አድረገናል። ሌሎች ቅርሶችን ከማስመለስም ባሻገር፣ እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ ሆኖ፣ ወደፊት ጎንደር ውስጥ የጎንደር ድል በዓልንም ማክበር እንፈልጋለን።

ሁሉም በጊዜው እንደሚሆን ባለ ሙሉ ተስፋ ነኝ!

በድጋሚ እንኳን ለመቶኛ ዓመት የጎንደር ሆስፒታልና ሰባኛ ዓመት የጎንደር ዮኒቨርስቲ ምስረታ በዓል አደረሰን! ለሁላችሁም መልካም ምሽት እመኝላችኋለሁ፣ ለተሰጠኝም ዕድል አመሰግናለሁ።

እግዚአብሔር አገራችንንና ሕዝባችንን ይባርክልን፣ ኢትዮጵያንም ይጠብቅልን።

ደህና አምሹ፣ አመሰግናለሁ።